1. መግቢያ

መምህራንና የት/ቤት አመራሮች የሙያ ፈቃድ ለማግኘት ከሚመዘኑባቸው መሳሪያዎች አንዱ በሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች መሰረት ያደራጁትን ማህደረ ተግባር መገምገምና ውጤት መስጠት መሆኑን በሙያ ፈቃድ የማስፈጸሚያ መመሪያ ላይ ተቀምጧል። የመምህራንና የት/ቤት አመራሮች ማህደረ ተግባር በት/ቤቶች የተለያየ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማርካት በሚያደርጉት ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የፈጸሙትን ተግባርና ያስመዘገቡትን ውጤት በግልጽ የሚያሳይ ማስረጃ ነው። ማህደረ ተግባር ዕቅዶችን፣ በውጤታማነት የተከናወኑ ተግባራትን፣ የተካሄዱ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችንና የመጡ ለውጦችን እንዲሁም ከት/ቤቱ ማህበረሰብና ሌሎች ባለድርሻዎች ጋር ስላላቸው ውጤታማ የስራ ግንኙነት የተደረገ ግምገማና የታዩ መሻሻሎችን የያዙ ሰነዶችን ያጠቃልላል።

መምህራንና የት/ቤት አመራሮች በሀገር አቀፍ የመምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሙያ ብቃት ስታንዳርዶች እና ንዑሳን ስታንዳርዶች መሰረት ያደራጇቸውን የክንውን ማህደረ ተግባራት በመመርመር ብቃታቸውን በትክክልና በግልጽ ሊያሳዩ የሚያስችሉ መሆኑን ለመገምገምና ውሳኔ ለመሥጠት ይህ የማህደረ ተግባር ምዘና ሰነድ ተዘጋጅቷል። ሰነዱ መግቢያ፣ የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና ዓላማዎች፣ የምዘና መረጃ ምንጮች፣ የምዘና አፈጻጸምና የምዘና ፎርማቶችን ይዟል።

2. የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና አስፈላጊነት

የመምህራንና የት/ቤት አመራሮችን ሙያዊ ብቃት ለማረጋገጥ በሚደረገው ምዘና የክንዋኔ ማህደረ ተግባር በጽሑፍ ምዘና የማይለኩትን ብቃቶች ለመመዘን እና በንድፈ ሃሳብ የሚያዉቁትን ምን ያህል በተግባር መተርጎም እንደሚችሉ ለመመዘንም ያስችላል። መምህራንና የት/ቤት አመራሮች ዕውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውንና አቀራረባቸውን በመጠቀም ተግባራትን ከተቀመጠው መስፈርት ጋር በማገናዘብ እያከናወኑ በየጊዜው እራሳቸውን ለማብቃትና ለመማር ማስተማር ስራው ስኬታማነት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግ ይጠቅማል። በአጠቃላይ የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና መምህራንና የት/ቤት አመራሮች የመማር ማስተማር ሂደቱን ለመምራት፣ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግና ተግባራትን በውጤታማነት ለማከናወን ያላቸውን ብቃት በመለካት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት አስፈላጊ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ያስችላል።

3. የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና ዓላማ

የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና ዋና ዓላማ መምህራንና የት/ቤት አመራሮች ዕውቀት፣ ክህሎትና አስተሳሰባቸውን አቀናጅተው በስታንዳርድ መሰረት ተግባራትን የማከናወን ብቃታቸውን ማረጋገጥ ነው።

የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

- መምህራንና የት/ቤት አመራሮች ተግባሮቻቸው በሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች መሰረት እንዲፈጽሙ ለማስቻል፣
- መምህራንና የት/ቤት አመራሮች የሙያ ፈቃድ ለማግኘት ሲያመለክቱ ውሳኔ ለመስጠት መረጃዎችን ለመጠቀም፣
- መምህራንና የት/ቤት አመራሮች የራሳቸውንና የተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት አቅደው ብቃታቸውን በተከታታይና በማያቋርጥ ሁኔታ ለማሳደግ እንዲችሉ ግብዓት ለመስጠት፣
- በየጊዜው የደረሱበትን ሙያዊ እድገት ለመገምገምና ለማሻሻል እንዲችሉ ለማድረግ፣
- በመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ተደራጅተው የተያዙ የተግባራት ክንውን ውጤቶች የሚያሳዩ ሰነዶች በመነሳት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ

4. የክንዋኔ ማህደረ ተግባር የመረጃ ምንጮች

4.1. አጠቃላይ የግል መረጃ

4.1.1 ለመምህራን

1. ስም ---------- የአባትስም----------የአያት ስም----------

2. ዕድሜ ---------- 3. ጾታ---------- 4.የሚሰሩበት፡- ክልል----------

ዞን/ክፍለ ከተማ ---------- ወረዳ----------ት/ቤት---------- የት/ቤት ደረጃ----------

5.የተመዘገ መለያ ቁጥር ----------

6. የመምህሩ/ሯ የት/ደረጃ ----------

7. የተመረቀበት የትምህርት ዓይነት፡- በዲፕሎማ ---------- በዲግሪ ---------- በ 2ኛ ዲግሪ--------

8. የተመረቀበት ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ ----------

9. የቅጥር ዘመን /ቀን፣ ወር፣ ዓ.ም/----------

10. አገልግሎት ----------

11. የሚያስተምሩት የት/ዓይነት----------

12. የመምህሩ/ሯ የደረጃ ዕድገት መሰላል ----------

13.መምህሩ/ሯ የሚወዳደሩበት የሙያ ፈቃድ ዓይነት----------

14. ስልክ ቁጥር፡- ሞባይል ---------- መደበኛ ----------

15. የኢሜል አድራሻ ----------

4.1.2 ለት/ቤት አመራሮች

1. ስም ----------የአባትስም---------- የአያት ስም----------

2. ዕድሜ ---------- 3. ጾታ---------- 4.የሚሰሩበት፡- ክልል----------

ዞን/ክፍለ ከተማ ---------- ወረዳ----------

ት/ቤት----------የት/ቤት ደረጃ---------- 5.የተመዛኝ መለያ ቁጥር ----------

6. የት/ቤት አመራሩ/ሯ የትምህርት ደረጃ ---------- 7. የተመረቀበት የትምህርት ዓይነት፡ በዲፕሎማ ---------- በዲግሪ ---------- በ 2ኛ ዲግሪ----------

8. የተመረቀበት ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ ----------

9. የቅጥር ዘመን /ቀን፣ ወር፣ ዓ.ም/----------

10.የት/ቤት አመራርነት ሥልጠና ስለመውሰዱ/ዷ፡- ወስዷል---------- አልወሰደም ------

11. የስራ ድርሻ ---------- 12. አገልግሎት ----------

13. የት/ቤት አመራሩ/ሯ የደረጃ ዕድገት መሰላል ----------

14. የት/ቤት አመራሩ/ሯ የሚወዳደሩበት የሙያ ፈቃድ ዓይነት----------

15. ስልክ ቁጥር ሞባይል ---------- መደበኛ ----------

16. የኢሜል አድራሻ ----------

4. 2. የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና የመረጃ ምንጮች

4.2.1 የመምህራን የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና የመረጃ ምንጮች

1 ሙያዊ ብቃት፡- ውጤታማ የመማር ማስተማር ዕቅድ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ

1.1.እቅድ

- ✓ የትምህርት እቅድ (የእለት/የሳምንት/፣ የአመት)

1.2.መማር ማስተማር

- ✓ የተዘጋጁ ወርክሸቶች
- ✓ የሚያስተምረውን ትምህርት ተጨባጭ ለማድረግ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች(ቤተ ሙከራ፣ የመስክ ምልከታ፣ የዳኝነት ሂደት ምልከታ...)
- ✓ የተዘጋጀ የማስተማሪያ ኖት
- ✓ አካቶ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ስለመጠቀሙ የሚያሳይ ሰነድ
- ✓ በክፍል ምልከታ ግብረመልስ የተሰጠበት ሰነድ

2. *ሙያዊ ብቃት፡-አጋዥና አመች የትምህርት አካባቢ መፍጠርና ማስጠበቅ*

- ስለተማሪዎች የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ማጠቃለያ
- የመማሪያ ክፍል ደንብና መመሪያ
- የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎች ዝግጅትና አጠቃቀም የሚያሳይ ማስረጃ

3 *ሙያዊ ብቃት፡-የተማሪዎችን የትምህርት ክትትል አስመልክቶ ምዘናዎችን ማከናወን፣ ግብረ መልስ መስጠትና ሪፖርት ማድረግ*

- የተማሪዎች ውጤት የተጠናቀረበት፣ የተተነተነበትና ሪፖርት የቀረበበት/ግብረ መልስ የተሰጠበት ሰነድ
- መምህሩ የሚያወጣቸው ቴስቶችና ተከታታይ ምዘናዎች ናሙና
- ተማሪዎች በቡድን የሰሩት የጽሁፍ ስራ
- ስለተማሪዎች ውጤት ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር የተደረገ ውይይት ቃለጉባኤ፣
- በተማሪዎች የትምህርት ሂደት ላይ የተሰጠ ገንቢና ወቅታዊ ግብረ መልስ

4. *ሙያዊ ብቃት፡-* በሙያ ማሻሻያ ትምህርትና ስልጠና መሳተፍ

- የአመቱ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ/የተሙማ/ እቅድና ድርጊት መርሃ ግብር
- የተሙማ ትግበራ ሪፖርትና ጽብረቃ
- ከሙያ ባልደረባዎቹ ጋር በጋራ በመስራት የመጣ አሰራር መሻሻል የሚያሳይ ማስረጃ

5.*ሙያዊ ብቃት፡ ከወላጆችና ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው ግንኙነት/ከስራ ባልደረባዎች፣ ከወላጆች /አሳዳጊዎችና ከማህበረሰቡ ጋር ሙያዊ ተሳትፎ ማድረግ*

- ስለተማሪዎች ባህሪ ከወላጆች ጋር የተደረገ ውይይት ቃለጉባኤ
- **የመምህርነት ስነምግባር የማሟላት ብቃት**

4.2.2 የር/መምህራን የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና **የመረጃ ምንጮች**

ሙያዊ ብቃት **1፡-** *የመማር ራዕይ አመራርና አስተዳደር*

- በት/ቤት ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕቅድ ዝግጅት ሂደት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማረጋገጫ ሰነዶች/ የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች
- የተዘጋጀ የትምህርት ቤት መሪ ዕቅድ
- የባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የተገመገመ ዕቅድ አፈጻጸምና የተከለሰ ዕቅድ

ሙያዊ ብቃት 2፡- የት/ቤትና ማሕበረሰብ ግንኙነትና ተሳትፎ አመራር

- የአካባቢውን ማህበረሰብና ት/ቤቱን ለማስተሳሰር የተጠናከረና ወደ ስራ የገባ ወመህ/ ወተመህ ስለመኖሩ ማስረጃ
- በት/ቤቱ የልማት ስራዎች የተሳተፉ ባለድርሻዎች ማስረጃ
- ከወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ የተገኘ ድጋፍ ማስረጃ
- ከማሕብረሰብ የተገኘው ሀብት ለመማር ማስተማር ስራ ላይ መዋሉን የሚያሳይ ሰነድ

ሙያዊ ብቃት 3፡- የመማር ማስተማር አመራርና አስተዳደር

- የመማር ማስተማር ስነ ዘዴዎችና ቅጻቅጾች ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የተካሄደ ክትትልና ድጋፍ ማስረጃ
- የተማሪዎች ተከታታይ ምዘና የተካሄደባቸው ሰነዶች
- ስለጥናትና ምርምር ከመምህራን ጋር የተደረገ ውይይት ቃለጉባኤ
- የተካሄዱ ጥናትና ምርምሮች የሚያሳይ ሰነድ
- የጥናትና ምርምር ግኝቶችን ለባለድርሻዎች በማስተዋወቅ ወደ ትግበራ ስለመገባቱ ማስረጃ
- ልዩ የትምህርት ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች መረጃ አደራጅቶ በመያዝ የተደረገ ድጋፍ ማስረጃ
- ከት/ቤት ያቋረጡ ተማሪዎች መረጃ
- በዚያው ክፍል የደገሙ ተማሪዎች መረጃ
- የተማሪዎች ውጤት ማጠራቀሚያና ትንተና የተሰራበት ሰነድ
- የውስጥ ሱፐርቪዥን ተካሂዶ ግብረ መልስ የተሰጠበት ሰነድ

ሙያዊ ብቃት **4፡-** የግለሰቦችና የቡድን አቅም ግንባታና አመራር

- ለራሱና ለሌሎች የተካሄደ የአቅም ግንባታ ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ሰነድ
- በተለየው የአቅም ክፍተት መሰረት የተሰጡ ስልጠናዎች ማስረጃ
- የተከታታይ *ሙያ* ማሻሻያ/ተሙማ/ ዕቅድና ትግበራ
- በተሙማ ትግበራ ላይ የተሰጠ ድገፍና ግብረ መልስ
- የተከታታይ *ሙያ* ማሻሻያ አፈጻጸም ሪፖርትና ጽብረቃ
- በተሙማ አስተባባሪ የተሰጠ ግብረመልስ

ሙያዊ ብቃት **5፡-**የትም/ቤት ሥራ ክንውን፣ የሀብት አመራርና አስተዳደር

- የመማር ማስተማር አካባቢን ምቹና ማራኪ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች የሚያረጋግጡ ሰነዶች፣
- ከት/ቤቱ የተለያዩ የቡድን *መሪዎች* ጋር የተካሄዱ ውይይቶች ቃለጉባኤ/ ሪፖርት
- የተፈጠረ የውስጥ ገቢ ምንጭና የተገኘ ሃበት ሪፖርት
- የተዘጋጀና ተግባር ላይ የዋለ የሀብት ማፈላለጊያ ፕሮጀክት
- የተገኘው ሀብት ስራ ላይ መዋሉን የሚያሳይ ማስረጃ
- የት/ቤቱ የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም፣ የበጀት ዕቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለት/ቤት ማህበረሰብ፣ ለወላጆችና ለአካባቢው ህብረተሰብ ማቅረቡን የሚያሳይ ሰነድ
- የት/ቤት ደንቦችና *መመሪያዎች* ቅጅ

4.2.3 የሱፐርቫይዘሮች የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና የመረጃ ምንጮች

ሙያዊ ብቃት 1፦ የትምህርት ቤት እቅድ ዝግጅትን መደገፍ

- የት/ቤት ራእይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶችና እቅድ ሲዘጋጅ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ የሚያሳይ ሰነድ
- የት/ቤቶች የስራ ዕቅድ የመማር ማስተማርን ማዕከል አድርጎ እንዲታቀድ የተደረገ ድጋፍ የሚያሳይ ማስረጃ
- በዕቅድ ዝግጅት ላይ የተደረጉ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤዎች

ሙያዊ ብቃት 2፦ ለጥናትና ምርምር ት/ቤቶችን ማነሳሳት፣ ማካሄድና መምራት

- የጥናትና ምርምር ስትራቴጂን በማዘጋጀት ከመምህራንና ርዕሰ መምህራን ጋር የተደረገ ውይይት ቃለ ጉባኤ
- የጥናትና ምርምር ቴክኒኮች ተለይተው የተደረገ ገለጻና ስልጠና የሚያሳይ ሰነድ
- በመምህራን፣ ር/መምህራንና በራሱ የተካሄዱ ጥናትና ምርምር ሰነዶች
- በጥናትና ምርምር ሂደት የተሰጠ ድጋፍ
- የተሰሩ ጥናትና ምርምሮችን ለባለድርሻዎች የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን የሚያሳይ ሰነድ
- በጥናቱ ግኝቶች መሰረት ወደ ትግበራ እንዲገባ የተደረገ ሙያዊ ድጋፍ ማስረጃ

ሙያዊ ብቃት 3፦ በተግባራት ክንውኖች ሂደት ወቅታዊ እውቀትንና ግንዛቤን ጥቅም ላይ ማዋል

- የተዘጋጁ የክትትልና ግምገማ ዕቅዶችና መርሃግብሮች የሚያሳይ ሰነድ
- በት/ቤቶች የተገመገሙ ወቅታዊ የትምህርት ስራዎችን የሚያሳይ ማስረጃ
- የተቀየሱና የተተገበሩ አዳዲስ አሠራሮች ማስረጃ
- የተደረገ ክትትል፣ ድጋፍና ግብረ መልስ የሚያሳይ ሰነድ

ሙያዊ ብቃት 4፦ ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደርን መተግበር

- የሚካሄዱ ውይይቶችና የሚሰጡ ውሳኔዎች የት/ቤቱን ማህበረሰብ አሳታፊ መሆናቸውን ያረጋገጠበት ቃለጉባኤ
- ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት ለማረጋገጥ ለመምህራንና ር/መምህራንየተደረገ ክትትልና ድጋፍ ማስረጃ፣
- ቀጣይነት ያለው መሻሻልን፣ ፈጠራንና ለውጥን ለመምራት የተቀየሱ ስትራቴጂዎች ማስረጃ

ሙያዊ ብቃት 5፦በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ አስፈላጊ አሰራሮችና ግብዓቶች መለየትና መተግበር

- የተለዩ የት/ቤት ደንቦች፣ አሰራሮችና ግብዓቶች
- ህብረተሰቡንና ሌሎች ባለድርሻዎችን በማወያየት የተጓደሉትን ግብዓቶች ለማሟላት የተገኘ ድጋፍ ማስረጃ
- በተያዘው ዕቅድ መሰረት ደረጃ በደረጃ የተሟሉ ደንቦች፣ አሰራሮችና ግብዓቶች

ሙያዊ ብቃት **6**፦ ራስን፣ ግለሰብንና ቡድንን ማብቃት

- የተለዩ የሥልጠና ፍላጎቶችን ዳሰሳ ጥናት የያዘ ሰነድ
- በተለዩ ፍላጎቶች መሰረት የተሰጠ የአቅም ግንባታ ስልጠና
- የተሙማ ዕቅድ፣ ትግበራ ሪፖርትና ጽብረቃ ሰነድ፣
- በተሙማ ለመምህራንና ር/መምህራን የተደረገ ድጋፍና ግብረ መልስ

5. የመምህራንና የት/ቤት አመራሮች የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና አፈጻጸም

5.1 የምዘናው ሂደት

መምህራንና የት/ቤት አመራሮች የሙያ ፈቃድ ለማግኘት በየሙያዊ ብቃት ስታንዳርዳቸው መሰረት ይመዘናሉ። ለዚህ የሙያ ብቃት ምዘና ከምንጠቀምባቸው የምዘና መሳሪያዎች አንዱ ማህደረ ተግባር ነው። ማህደረ ተግባር የመምህሩንና የት/ቤት አመራሩን ስራዎች በግልጽ ሊያሳዩ የሚችሉ የተመረጡ ማስረጃዎች ስብስብ ነው። የመምህራንና የት/ቤት አመራሮችን ማህደረ ተግባር ምዘና የሚያካሂድ ቡድን በወረዳና በት/ቤት ደረጃ/ ይዋቀራል።

ምዘናውን የሚያካሂደው ቡድን ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችና የግል መገለጫዎች በማህደረ ተግባሩ ውስጥ መኖራቸውን ያረጋግጣል። የሰነዶችን ዓይነት የሚገልጽ ርዕስና የተዘጋጁበት ቀንና ዓመተ ምህረት ሊኖረዉ ይገባል። በማህደረ ተግባር ውስጥ የተሰበሰቡትና የተደራጁት መረጃዎች ግልጽ፣ ወቅታዊ፣ ምዘናው ከሚካሄድበት ወቅት በፊት ባሉት ሁለት መንፈቀ ዓመት የተሰሩና በቅርብ የስራ ኃላፊ የተረጋገጡ መሆን አለባቸው። ሆኖም ግን ስራው ተጀምሮ እስከ ሚጠናቀቅ ከአንድ ዓመት በላይ የሚወስድ ከሆነ ስራው ተጀምሮ የተጠናቀቀበትን ጊዜ በጥንቃቄ በማጤን ምዘናው እስከ ሚካሄድበት ጊዜ ላሉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ሊያዝ ይችላል።

የተሰበሰቡት መረጃዎች ለማህደረ ተግባር ምዘና በተዘጋጀው ፎርማት ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ይደራጃሉ። ፎርማቶቹ የተዘጋጁት በመምህራንና የት/ቤት አመራሮች ሙያዊ ብቃቶችና በስራቸው በተቀመጡ ንዑሳን ብቃቶች መሰረት ነው። እያንዳንዱ ሙያዊ ብቃትና በስሩ የተቀመጡ ተግባራት ለመማር ማስተማሩ ሂደት መሳካት ከሚኖቸው ሚና አንጻር ክብደት ተሰጥቷቸዋል። የምዘና ቡድኑ የተሰበሰቡትን መረጃዎች እየፈተሸ ለተመዛኝ መምህራንና የት/ቤት አመራሮች ውጤት ይሰጣል።

የምዘና ቡድኑን ውጤትና ውሳኔ አሰጣጥ ፍትሃዊና ወጥነት ያለው ለማድረግ ይህ የማህደረ ተግባር ማስፈጸሚያ ሰነድ ተዘጋጅቷል። ለተመዛኝ መምህራንና የት/ቤት አመራሮች ስለሙያ ፈቃድ ምዘና የማህደረ ተግባር አዘገጃጀት፣ መረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል። የመዛኝ ቡድን አባላትም በምዘና መስፈርቱ፣ በሚታዩ መረጃዎችና በአጠቃላይ የምዘናው ሂደት ላይ ስልጠና ይሰጣል። ይህም በመዛኝ ቡድኖች መካከል የሚከሰተውን የአመዛዘን ልዩነት ለማጥበብና ተዓማኒነትን ከፍ ለማድረግ ያግዛል። በተጨማሪም መምህራንና የት/ቤት አመራሮች የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ላይ በተቀመጡት ተግባራት መሰረት ራሳቸውን በመምራት ተግባሮቻቸውን እንዲፈጽሙና ማስረጃዎቻቸውን እንዲያደራጁ ብሎም ሙያዊ ብቃታቸውን እንዲያሻሽሉ ያግዛል።

5.2 የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና ቡድን

የመምህራንና የት/ቤት አመራሮችን የክንዋኔ ማህደረ ተግባር መረጃዎች በማየት ምዘና የሚያካሂዱ 5 አባላት ያሉት ቡድን በወረዳና በት/ቤት ደረጃ ይቋቋማል።

5.2.1 የመምህራን የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና

በመምህራን የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችን በማየት ምዘና የሚያካሂዱ 5 አባላት ያሉት ቡድን በት/ቤት ደረጃ ይቋቋማል። ይኸውም፦

1. ርዕሰ መምህር----------ሰብሳቢ
2. ም/ር/መምህር ወይም ዩኒት አስተባባሪ---------- አባል
3. የመሰረታዊ መምህራን ማህበር ሰብሳቢ---------- አባል
4. የተሙማ አስተባባሪ----------አባል
5. የተመዛኙ መምህር ትም/ ክፍል ተጠሪ---------- አባልና ጸሐፊ

- የትምህርት ክፍል ተጠሪ መምህር በሚመዘንበት ጊዜ በሱ ምትክ የተሻለ አገልግሎት ያለው መምህር ተመድቦ ከመዛኝ ቡድኑ ጋር ይሰራሉ።
- የመሰረታዊ መምህራን ማህበር ሰብሳቢ በሚመዘንበት ጊዜ በሱ ምትክ የማህበሩ ጸሐፊ ተመድቦ ከመዛኝ ቡድኑ ጋር ይሰራሉ።
- የተሙማ አስተባባሪ በሚመዘንበት ጊዜ በሱ ምትክ የት/ቤቱ የውስጥ ሱፐርቪዥን ቡድን ተጠሪ ተመድቦ ከመዛኝ ቡድኑ ጋር ይሰራሉ።

5.2.2 የርዕሰ መምህራን የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና

ሀ/ ርዕሰ መምህር የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና

በር/መምህራን የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችን በማየት ምዘና የሚያካሂዱ 5 አባላት ያሉት ቡድን ይቋቋማል። ይኸውም፦

1. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማው የመም/ት/ቤት አመራር ሙያ ፈቃድ ተጠሪ -----ሰብሳቢ
2. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማው የመም/ት/ቤት አመራር ልማት ተጠሪ ----------አባል
3. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማውመምህራን ማህበር ሰብሳቢ----------አባል
4. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማው የትምህርት ጥራት የስራ ሂደት ተጠሪ----------አባል
5. የት/ቤት ሱፐርቫይዘር ----------አባልና ጸሐፊ

ለ/ ም/ር/መምህር የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና

በም/ር/መምህራን የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችን በማየት ምዘና የሚያካሂዱ 5 አባላት ያሉት ቡድን ይቋቋማል። ይኸውም፦

1. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማው የመም/ት/ቤት አመራር ሙያ ፈቃድ ተጠሪ------ሰብሳቢ
2. ርዕሰ መምህር----------አባል
3. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማው የትምህርት ጥራት የስራ ሂደት ተጠሪ----------አባል
4. የወረዳው/የክ/ከተማው መምህራን ማህበር ሰብሳቢ----------አባል
5. የት/ቤት ሱፐርቫይዘር----------አባልና ጸሐፊ

5.2.3 የት/ቤት ሱፐርቫይዘሮች የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና

የት/ቤት ሱፐርቫይዘሮች የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና እንደ ተጠሪነቱ ከወረዳ/ ከዞን/ ከክፍለ ከተማ በተውጣጡ የቡድን አባላትይሆናሉ። በመሆኑም፡-

1. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማው የመም/ት/ቤት አመራር ሙያ ፈቃድ ተጠሪ----ሰብሳቢ
2. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማው የመም/ትምህርት አመራር ልማት ተጠሪ------- -አባል
3. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማው ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ተጠሪ---------- አባል
4. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማውመምህራን ማህበር ሰብሳቢ---------- ----------አባል
5. የወረዳው/የዞኑ/የክ/ከተማው የትምህርት ጥራት ተጠሪ ----------አባልና ጸሐፊ

5.3 የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና ፎርማት

ማህደረ ተግባር የመምህራንና የት/ቤት አመራሮችን አንኳር አንኳር ስራዎች የሚያሳይ የመረጃዎች ስብስብ ነው።ማህደረ ተግባር ማደራጀት ለተለያዩ ዓላማዎች ይጠቅማል። በመሆኑም ለሙያ ፈቃድ ምዘና በማህደረ ተግባር ውስጥ የሚካተቱ ሰነዶች የአፈጻጸም ብቃትን የሚያመለክቱ እንጂ ሁሉንም ዓይነት መረጃዎች የያዙ አይደሉም። ስለሆነም በክንዋኔ ማህደረ ተግባር ውስጥ የሚካተቱ ዝርዝር መረጃዎች በመምህራንና የት/ቤት አመራሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች/በተዘጋጀው ፎርማት/ ውስጥ ያሉትን ተግባራትና አፈጻጸሞች የሚያሳዩ ናቸው።

5.3.1 የመምህራን የክንዋኔ ማህደረ ተግባምዘና ፎርማት

ተ.ቁ.	ሙያዊ ብቃት /ተግባራት		ንኡስ ብቃቶች/ተግባራት	የንዑስ ብቃት ክብደት	የንዑስ ብቃት ውጤት	የመረጃ ምንጮች	አስተያየት
1	ውጤታማ የመማር ማስተማር ዕቅድ ማዘጋጀትእና ተግባራዊ ማድረግ (7 ነጥቦች)	1.1 ማቀድ (2 ነጥቦች)	እቅዱን አካቶና አሳታፊ፤ ይዘቱን ከመማር ማስተማር ስነዘዴውና ከምዘናው ጋር የተሳሰረ የማድረግ ብቃት	2		➢ የትምህርት እቅድ (የአለት/የሳምንት ፣የአመት)	
		1.2 መማር ማስተማር (5 ነጥቦች	አካቶና አሳታፊ፣ አዎንታዊ ግንኙነትና መስተጋብር ያለው የመማር ማስተማር ስትራቴጂ የመጠቀም ብቃት	2		➢ የተዘጋጀ የማስተማሪያ ኖት ➢ የተዘጋጀ ወርክሽት፣ ➢ የሚያስተምረውን ትምህርት ተጨባጭ ለማድረግ የተጠቀመ ባቸው ዘዴዎች(ቤተ ሙከራ፣ የመስክ ምልከታ፣ የዳኝነት ሂደት ምልከታ...) ➢ በክፍል ምልከታ ግብረ መልስ የተሰጠበት ሰነድ	
			የተለያዩ የመማር ማስተማር ስነ ዘዴዎች በመጠቀም የተማሪዎቹን ጥልቅ አስተሳሰብና ችግር ፈቺነት ክህሎት የማሳደግ ብቃት	2		➢ የተለያዩ የማስተማሪያ ስነ ዘዴዎች ስለመጠቀሙ የሚያሳይ ሰነድ	
			የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሀፍት ግምገማ የማድረግ ብቃት	1		➢ የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሀፍት የግምገማ ሪፖርት	
	ድምር			7			
2	አጋዥና ምቹ የትምህርት አካባቢ መፍጠርና ማስጠ በቅ (3 ነጥቦች)		*የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ምቹ የመማሪያ አካባቢ የመፍጠር ብቃት*	1		➢ የመማሪያ ክፍል መመሪያና ደንቦች ➢ የተለዩና የሚጠቀሙባቸው አሳታፊ የመማር ማስተማር ስነ ዘዴዎች ሰነድ	
			የክፍል ውስጥ ተግባራትን የመምራት ብቃት	1		➢ ስለተማሪዎች ባህሪያት የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ማጠቃለያ	
			የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የማዘጋጀትና የመጠቀም ብቃት	1		➢ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎች ዝግጅትና አጠቃቀም የሚያሳይ ማስረጃ	
ድምር				3			

ተ	ሙያዊ ብቃት	ንኡስ ብቃቶች/ተግባራት	የንዑስ	የንዑስ	የመረጃ ምንጮች	አስተያየት

.ቁ.			ብቃት ክብደት	ብቃት ውጤት		
3	የተማሪዎችን የትምህርት ምዘናዎች ማከናወን፣ ግብረ መልስ መስጠትና ሪፖርት ማድረግ (3 ነጥቦች)	*የተማሪዎችን የመማርና የውጤት እድገት ለመለካት የተለያዩ መረጃዎችን መሰብሰብና የመተንተን ብቃት*	1		➢ የተማሪዎች ውጤት ማስፈሪያ ➢ የተማሪዎችን ውጤት ለውጥ የሚያሳይ ሪፖርት,	
		የተማሪዎችን ውጤት ለማሳደግ የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን የመጠቀም ብቃት	1		➢ መምህሩ የሚያዘጋጃቸው ቴስቶችና ተከታታይ ምዘናዎች ናሙና	
		ወቅታዊና ተገቢ የሆነ ግብረ መልስ የመስጠት ብቃት	1		➢ ተማሪዎች ለሰሩት ስራ በጽሁፍ የተሰጠ አስተያየት ➢ በተማሪዎች የትምህርት ሂደት ላይ የተሰጠ ገንቢና ወቅታዊ ግብረ መልስ	
ድምር			3			
4	በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር መሳተፍ (5 ነጥቦች)	የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ /ተሙማ/ ዕቅድና የድርጊት መርሃ ግብር የማዘጋጀት ብቃት	1		➢ የዓመቱ የተሙማ እቅድና ትግበራ የድርጊት መርሃ ግብር	
		የተሙማ የክንውን ጽብረቃ የማቅረብ ብቃት	2		➢ የተሙማ የአመቱና የመንፈቅ አመቱ የአፈጻጸም ሪፖርት ➢ የተሙማ አመቻች ግብረ መልስ	
		የመማር ማስተማር ችግር መፍቻ ጥናት የማድረግ ብቃት	1		➢ የተሰራ ወቅታዊ ችግር መፍቻ ጥናታዊ ጽሁፍ	
		የጥናቱን ግኝት በተግባር ላይ የማዋል ብቃት	1		➢ በመማር ማስተማሩ ሂደት የታየ ለውጥ ማስረጃ	
ድምር			5			
5	ከስራ ባልደረባዎች፣ ከወላጆች/ከአሳዳጊ ዎችና ከማህበረሰቡ ጋር ሙያዊ ተሳትፎ ማድረግ	በተማሪዎች ስነምግባር መሻሻል ከወላጆች/ አሳዳጊዎች ጋር ተገቢውን ውይይት የማድረግ ብቃት	1		➢ በተማሪዎች ውጤትና ስነ ምግባር ከተማሪዎች፣ ከስራ ባልደረባዎችና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር የተደረገ ውይይት ቃለጉባኤ	
		የመምህርነት ስነምግባር የማሟላት ብቃት	1		የመምህርነት ሙያዊ ስነምግባር ችግር የሌለበት ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ	
የዚህ ብቃት ድምር			2			
ጠቅላላ ድምር			20			

5.3.2 የርዕሰ መምህራን የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና ፎርማት

ተ.ቁ	የሙያ ብቃት	ንዑሳን ብቃቶች	የንዑስ ብቃት	የንዑስ ብቃት	የመረጃ ምንጮች	አስተያየት

			ክብደት	ውጤት		
1	የመማር ማስተማር ራዕይ አመራርና አስተዳደር (3 ነጥብ)	የጋራ ራዕይ በማውጣትና ባለድርሻዎችን በማስገንዘብ ተግባራዊ የማድረግ ብቃት	1		• በት/ቤት ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕቅድ ዝግጅት ሂደት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማረጋገጫ ሰነዶች	
		የትምህርት ቤት ዕቅድ ግቦች ዝግጅት ሂደቶችን የመምራት ብቃት	1		• የተዘጋጀ የትምህርት ቤት መሪ ዕቅድ	
		ለተከታታይ መሻሻልና ዕድገት የለውጥ ሂደቶችን የመምራት ብቃት	1		• የባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የተገመገመ ዕቅድ አፈጻጸምና የተከለሰ ዕቅድ	
	ድምር		**3**			
2	የሕብረተሰብ ተሳትፎና የት/ቤት ግንኙነት አመራር (3 ነጥብ)	ወላጆች፣ የአካባቢው ማህበረሰብና ሌሎች አጋር አካላት ከት/ቤቱ ጋር የማስተሳ ሰርና ግንኙነታቻን የማጠናከር ብቃት	1		• የአካባቢውን ማህበረሰብና ት/ቤቱን ለማስተሳሰር የተጠናከረና ወደ ስራ የገባ ወመህ/ወተመህ ስለመኖሩ ማስረጃ	
		ወላጆች፣ የአካባቢውማህበረሰብና ሌሎች አጋር አካላት በትምህርት ቤት መሻሻልዕቅድ ትግበራ የማሳተፍ ብቃት	1		• በት/ቤቱ የልማት ስራዎች የተሳተፉ ባለድርሻዎች የሚያሳይ ሰነድ • ከወላጆች፣ የአካባቢው ማህበረሰብና አጋር አካላት የተገኘ ድጋፍ መረጃ	
		ከማሕበረሰቡ የተገኘውን ሀብት ለት/ ቤት መሻሻል መርሃ ግብር የመጠቀም ብቃት	1		• ከማሕበረተሰብ የተገኘው ሀብት ለመማር ማስተማር ስራ ላይ መዋሉን የሚያሳይ ሰነድ	
	ድምር		**3**			
3	የመማር - ማስተማርአመራርናአስተዳደር (6 ነጥብ)	የመማርማስተማርትግበራውጤታማነትን የማረጋገጥ ብቃት	2		• የመማር ማስተማር ስነ ዘይዎችና ቅጻቅጾች ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የተካሄደ ክትትልና ድጋፍ ሰነድ • ተከታታይ ምዘና የተካሄደባቸው ሰነዶች • ልዩ የትምህርት ፍላጐት ላላቸው ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍ ማስረጃ	
		በጥናትና ምርምር ስራ ላይ መምህራንን የማበረታታት፣ ጥናት የማካሄድና በግኝቶች መሰረት ወደ ተግባር የመግባት ብቃት	2		• ከመምህራን ጋር ጥናትና ምርምር ዙሪያ የተደረገ ውይይትና መግባባት ቃለጉባኤ • በራሱና በመምህራን የተካሄዱ ጥናትና ምርምር ግኝቶችን ለባለድርሻዎች በማስተዋወቅ ወደ ትግበራ መገባቱን የሚያሳይ ማስረጃ	
ተ.ቁ	የሙያ ብቃት	የሚከናወኑ ተግባራት (ንዑሳን ብቃቶች)	የንዑስ ብቃት ክብደት	የንዑስ ብቃት ውጤት	የመረጃ ምንጮች	አስተያየት
		የትምህርት ስራ መረጃዎችን የትም/ቤቱ ማህበረሰብ በአግባቡ እንዲጠቀምባቸው ሁኔታዎችን የማመቻቸት ብቃት	1		• ከት/ቤት ያቋረጡ ተማሪዎች መረጃ • የደገሙ ተማሪዎች መረጃ • የተማሪዎች ውጤት ማጠራቀሚያና ትንተና የተሰራበት ሰነድ	
		በመማር ማስተማር ጥራት ላይ ክትትልና ግምገማ የማድረግ ብቃት	1		• የውስጥ ሱፐርቪዥን ተካሂዶ ግብረ መልስ የተሰጠበት መረጃ • የሥርዓተ ትምህርት ግምገማ ስራ ክትትል ሪፖርት	

ድምር			**6**			
4	የግለሰብና የቡድን አቅም ግንባታ አመራር (4 ነጥብ)	በሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ክፍተቶችን የመለየት ብቃት	1		• ለየተካሄደ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ሰነድ	
		በተለየው ፍላጎት መሰረት ግለሰቦችንና ቡድኖችን ለማብቃት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ብቃት	1		• በተለየው የአቅም ክፍተት መሰረት የተሰጡ ስልጠናዎች የሚያሳይ ሰነድ	
		በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ /ተሙማ/ መሳተፍ፣ የመምህራንም አፈጻጸም የመከታተልና የመደገፍ ብቃት	2		• በተሙማ ትግበራ ላይ የሰጠው ድጋፍና ግብረ መልስ • የራሱ የተሙማ ዕቅድ፣ ትግበራ ሪፖርትና ጽብረቃ • በተሙማ አስተባባሪ የተሰጠው ግብረመልስ	
ድምር			**4**			
5	የትም/ቤት ሥራ ክንውንና ሀብት አመራርና አስተዳደር (4 ነጥብ)	የት/ቤት ማህበረሰብ አካላዊና አእምሮአዊ ፍላጐቶች የሚያሟላ የመማር ማስተማር አካባቢ የመፍጠርና የማጎልበት ብቃት	1		• የት/ቤት ደንቦችና መመሪያዎች ቅጅ • **የመማር ማስተማር አካባቢን ምቹና ማራኪ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች የሚያረጋግጡ ሰነዶች፣**	
		የመማር ማስተማር ሥራን ለማሳለጥ ሀብት ምንጭ የመፍጠርና የመጠቀም ብቃት	1		• የተፈጠረ የውስጥ ገቢ ምንጭና የተገኘ ሃበት ሪፖርት • የተዘጋጀና ተግባር ላይ የዋለ የሀብት ማፈላለጊያ ፕሮጀክት • የተገኘው ሀብት ስራ ላይ መዋሉን የሚያሳይ ማስረጃ	
		የትም/ቤቱን ሀብት አስተዳደርና አጠቃቀም የመምራትና **ለት/ቤት ማህበረሰብ፣ ለወላጆ ች፣ ለአካባቢው ህብረተሰብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት** የማሳወቅ ብቃት	2		• **የት/ቤቱን የሥራ አፈጻጸም፣ የበጀት ዕቅድና አፈጻጸም ሪፖርት፣** የት/ቤት ቁሳቁስ ለማሟላት የተያዘ ዕቅድና አፈጻጸም ሪፖርት **ለት/ቤት ማህበረሰብ፣ ለወላጆች፣ ለአካባቢው ህብረተሰብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ማቅረቡን የሚያሳይ ሰነድ**	
ድምር			**4**			
		ጠ/ድምር	**20**			

5.3.3 የሱፐርቫይዘሮች የክንዋኔ ማህደረ ተግባር ምዘና ፎረማት

ተ.ቁ	የሙያ ብቃት	የሚከናወኑ ተግባራት (ንዑሳን ብቃቶች)	የንዑስ ብቃት ክብደት	የንዑስ ብቃት ውጤት	የመረጃ ምንጮች	አስተያየት
1	የትምህርት ቤት እቅድ ዝግጅትንመደገ ፍ(4 ነጥብ)	መማር ማስተማርን የስትራቴጂክ እቅድ ማዕከል አድርጎ የማስቀመጥ ብቃት	2		➢ **የት/ቤቶች የስራ ዕቅድ የመማር ማስተማርን ማዕከል አድርጎ እንዲታቀድ የተደረገ ድጋፍ የሚያሳይ ሰነድ**	
		በት/ቤት የመማር ማስተማር ስትራቴጂ ክ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት ለት/ቤቶች ድጋፍ ክትትል የማድረግ ብቃት	2		➢ በራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶችና እቅድ ዝግጅት ወቅት ያደረጉትን ሙያዊ ድጋፍ የሚያሳይ ሰነድ	
ድምር			**4**			
2	ለጥናትና ምርምር ት/ቤቶችን መደገፍና ማበረታታት (3 ነጥብ)	የጥናትና ምርምር ስትራቴጂ በማዘጋጀት መምህራንና ር/መምህራን የማበረታታት፣ የመደገፍና የመምራት ብቃት	1		➢ የጥናትና ምርምር ስትራቴጂን በማዘጋጀት ከመምህራንና ር/መምህራን ጋር የተደረገ ውይይት ቃለ ጉባኤ ፣ ➢ በመምህራን፣ ር/መምህራንና በራሱ የተካሄዱ የጥናትና ምርምር	

					ሰነዶች	
		መምህራንና ር/መምህራን የተለያዩ የጥናትና ምርምር ቴክኒኮችን ተጠቅ መው ጥናት እንዲያካሂዱ የመደገፍ ብቃት	1		➢ በተለዩ የጥናትና ምርምር ቴክኒኮች ላይ የተደረገ ገለጻና ስልጠና ➢ በጥናትና ምርምር ሂደት የተሰጠ ድጋፍ	
		መምህራንና ርዕሰ መምህራን የጥናትና ምርምር ግኝቶችን ለባለድርሻዎች ለማስተዋወቅ ሁኔታዎችን የማመቻቸ ትና ሙያዊ ድጋፍ የማድረግ ብቃት	1		➢ የተሰሩ ጥናትና ምርምሮችን ለባለ ድርሻዎች የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን የሚያሳይ ሰነድ ➢ በጥናቱ ግኝት መሰረት ወደ ትግበራ እንዲገባ የተደረገ ድጋፍ መረጃ	
ድምር			**3**			
3	በመማር ማስተማር ትግበራ ሂደት ወቅታዊ እውቀትንና ግንዛቤን ጥቅም ላይ ማዋል (4 ነጥብ)	በትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደት የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረ መልስ ዕቅድና ፕሮግራም የማዘጋጀት ብቃት	2		➢ የተዘጋጁ የክትትልና ግምገማ ዕቅዶችና መርሃግብሮች የሚያሳይ ሰነድ	
		ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ተግባራት ክንውኖችን እንዲያሻሽሉ የመደገፍና የመገምገም ብቃት	2		➢ የተደረገ ክትትል፣ ድጋፍና ግብረ መልስ የሚያሳይ ሪፖርት ➢ የተገመገሙ ወቅታዊ የትምህርት ስራዎችን የሚያሳይ ሪፖርት ➢ የተቀየሱና የተተገበሩ አዳዲስ አሠራሮች ማስረጃ	
ድምር			**4**			

	የሙያ ብቃት	የሚከናወኑ ተግባራት (ንዑሳን ብቃቶች)	የንዑስ ብቃት ክብደት	የንዑስ ብቃት ውጤት	የመረጃ ምንጮች	አስተያየት
4	ውጤታማና አሳታፊ የት/ ቤት አመራርና አስተዳደርን ማስፈን (4 ነጥብ)	ለመምህራንና ርዕሰ መምህራን ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ አመራር እንዲሰጡ የማብቃት ብቃት	2		➢ ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት ለማረጋገጥ ለመምህራንና ር/መምህራን የተደረገ ክትትልና ድጋፍ ማስረጃ፣	
		ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አስዳደርን የማረጋገጥ ብቃት	2		➢ የሚካሄዱ ውይይቶችና የሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ የት/ቤቱ ማህበረሰብ አሳታፊ መሆናቸውን የሚያሳይ ቃለጉባኤ	
ድምር			4			
5	በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ ሰነዶች ና ግብዓቶች መለየትና መተግበር (2 ነጥብ)	ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ደንቦች፣ አሰራሮችና ግብዓቶች የመለየት ብቃት	1		➢ የተለዩ የት/ቤት ደንቦች፣ አሰራሮችና ግብዓቶች ዝርዝር ➢ ህብረተሰቡንና ሌሎች ባለድርሻዎች በማወያየት የተጓደሉትን ግብዓቶች ለማሟላት የተደረገ ድጋፍ ማስረጃ	
		በትምህርት ቤቶች የተጓደሉትን ደንቦች፣ አሰራሮችና ግብዓቶች የማሟላት ብቃት	1		➢ የተሟሉ ደንቦች፣ አሰራሮችና ግብዓቶች የሚያሳይ ሰነድ	
ድምር			2			
6	ራስን፣ ግለሰብንና ቡድንን መገንባት (3 ነጥብ)	የግለሰብና የቡድን የመማርና እድገት ፍላጎቶችን የመለየትብቃት	1		➢ የተለዩ የሥልጠና ፍላጎቶችንዳሰሳ ጥናት	
		ለራስ፣ ለግለሰቦችና ለቡድን የአቅም ግንባታ ሥራዎችን የማመቻቸትብቃት	1		➢ በተለዩ ፍላጎቶች መሰረት የተሰጠ የአቅም ግንባታ ስልጠና ማስረጃ	

		በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ/ተሙማ/ የመሳተፍ፣ የሌሎችንም አፈጻጸም የመከታተልናየመደገፍ ብቃት	1		➢ የራሱ የተሙማ ዕቅድ፣ ትግበራ ሪፖርት እና ጽብረቃ የያዘ ሰነድ፣ ➢ በተሙማ ለመምህራንና ር/መምህራን የተደረገ ክትትል፣ ድገፍና ግብረ መልስ	
ድምር			3			
ጠ/ድምር			20			